የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

፱ኛ ዓመት ቁጥር 1
፱th year No 1

ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም
HARAR Oct, 10 Th, 2004

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 5.00<br>Unit Price Br. 5.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box |

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 46/1997 ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ-መንግስትን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ---------------------------------------- ገጽ 369

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ- መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ-መንግስት ማዕደቂያ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ህገ-መንግሥቱን ስለማሻሻል

ጳጉሜ 6 ቀን 1987 የፀደቀዉ የክልሉ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ-መንግስት በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

### 3. ስለ ነባር ህጎች ተፈጻሚነት

በስራ ላይ ያሉ ህጎች ከተሻሻለዉ ህገ-መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

### 4. ሕገ-መንግሥቱ በስራ ላይ ስለሚዉልበት ጊዜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለዉ ህገ-መንግሥት ከመስከረም 30/1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ፕሬዝዳንት

## መግቢያ

እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሲደርስባቸዉ የነበረዉን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ባህላዊ ኃይማኖታዊ ጭቆና ጫናና ተጽእኖ በተለያየ ስልት መልክና ቦታ ሲታገሉ ቆይተዉ በመጨረሻ በግንቦት ወር 1983 ለዚሁ ሁሉ ምክንያት የሆነዉን ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ለመጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸዉን በራሳቸዉ ለማስተዳደር ታሪካቸዉ ባህላቸዉና ቋንቋቸዉን ለማዳበር በአጠቃላይ ብሔራዊ ህልዉናቸዉን ለመጠበቅ የሚያስችላቸዉን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ይህም ህዳር 29 ቀን 1987 በኢትዮጵያ ህዝቦች በጸደቀዉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት መረጋገጡን በመገንዘብ፣

የሐረሪ ህዝብ ምንም እንኳ በምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር፣ በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም በ1886 ዓ.ም በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛዉ ሥርዓት ሥር ከመዉደቁም በላይ ይህንን ስርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገዉ ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት ለእስራትና ብሎም ለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ መሆኑ የተነሳ ልዩ አወካከል ስልት ማስፈለጉን በመረዳት፣

የሐረሪ ሕዝብ ሲደርስበት የነበረዉን ግፍና ጭቆና ሲካፈሉ ከነበሩት ከአካባቢዉ የኦሮሞ ህዝብ እና ከሌሎች የክልሉ ነዋሪ ህዝቦች በመሆን የክልሉን አስተዳደር በጋራ ማቋቋምና መምራት ያለባቸዉ መሆኑን በማጤን፣

በክልላችን ዉስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለዉ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የግለሰብና የብሔር ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች የተከበሩበትና ከታሪካችን የወረስነዉን የተዛባ አመለካከትና ግንኙነት በማረምና

በማስተካከል መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለይም እኛ የሐረሪ፣ የኦሮሞና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር በተለይም ሦስቱን የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና በመካከላቸዉ የሚኖረዉን ግንኙነት በግልፅ ማስቀመጥና ተጠያቂነታቸዉንም በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በዚሁ መሰረት እኛ የሐረሪ ክልል ምክር ቤት አባላት የመረጠንን ህዝብ በመወከል ከዚህ በፊት ተመክሮበት የጸደቀዉንና በስራ ላይ ያለዉን የክልሉን ህገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክተን ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ የቀረበዉን ህገ መንግሥት መክረንበትና ተወያይተንበት ዛሬ መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ አጽድቀነዋል::

## ምዕራፍ 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ተብሎ የሚጠራ ዲሞክራሲያዊ መዋቅር ያለዉ መንግሥት በዚህ ህገ-መንግሥት ተመስርቷል::

### አንቀጽ 2

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ግዛት ወሰን

የሐረሪ ሕዝብ ክልል በሰሜን በኮምቦልቻና በጃርሶ ወረዳዎች በምስራቅ በጉርሱምና በባቢሌ ወረዳዎች በደቡብ በፈዲስ ወረዳና በምእራብ በአለማያ ወረዳ የሚዋሰን ነዉ::

### አንቀጽ 3

### ሰንደቅ ዓላማና አርማ

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ይኖረዋል:: ሰንደቅ አላማውም መደቡ ነጭ ሆኖ ከላይኛዉ ጠርዝ ገባ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ ቀይ መስመር ሲኖረው ከታችኛዉ ጠርዝ ከፍ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ አረንጓዴ መስመር ይኖረዋል::በቀዩና በአረንጎዴው መስመር መካከል ዓርማ ይኖረዋል::
2. የሰንደቅ ዓላማዉ ቀለማት የሚያስተላልፉት መልዕክት፣

   ሀ. ነጩ መደብ የክልሉ ሕዝብ በፍትህና በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ ሰላም ያለዉን ስሜትና ፍላጎት ያመለክታል፣

   ለ. ቀዩ መስመር ሕዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ ያደረገዉን ትግልና የከፈለዉን መስዋዕትነት ያመለክታል፣

   ሐ. አረንጓዴዉ መስመር ሕዝቡ ለልማትና ለዕድገት ቆርጦ መነሳቱንና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመለክታል::

### አንቀጽ 4

### የክልሉ መዝሙር

የሐረሪ ክልል ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲሁም የተገኘዉን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለዉን ምኞት የሚያንጸባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል:: ዝርዝሩን በህግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 5

### ርዕሰ ከተማ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ርዕሰ ከተማ ሐረር ነዉ::

### አንቀጽ 6

### የስራ ቋንቋ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የስራ ቋንቋ ሐረሪ እና ኦሮምኛ ናቸዉ::

### አንቀጽ 7

### የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-መንግሥት ዉስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገዉ የሴትንም ፆታ ያካትታል::

## ምዕራፍ ሁለት

## የህገ-መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

### አንቀጽ 8

### የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት

የሐረሪ ሕዝብ የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የህዝቡ የበላይነትም የሚገለጸዉ በዚህ ህገ-መንግሥት መሰረት በሚመርጣቸዉ ተወካዮችና ራሱ በሚያደርገዉ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነዉ::

### አንቀጽ 9

### የሕገ-መንግሥት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ:-

1. ይህ ህገ-መንግሥት የክልሉ የበላይ ህግ ነዉ:: ማንኛዉም ሕግ ልማዳዊ አሠራር ወይም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ዉሳኔ ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረዉም::
2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ የመንግሥት አካል የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸዉ ይህን ህገ-መንግሥት የማክበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸዉ::
3. በዚህ ህገ-መንግሥት ከተደነገገዉ ዉጪ በማናቸዉም አኳኋን የመንግሥት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነዉ::

### አንቀጽ 10

### ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰዉ ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸዉ::
2. በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸዉ::

## አንቀጽ 11

## የመንግሥትና የሀይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸዉ::
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም::
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም:: ኃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም::

## አንቀጽ 12

## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለህዝቡ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት::
2. ሕዝቡ በመረጠዉ ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታዉ ሊያነሳዉ ይችላል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል::
3. ማንኛዉም የሥራ ኃላፊ ወይም የህዝቡ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል::

## ምዕራፍ ሦስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች

## አንቀጽ 13

## ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛዉም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አዉጪ የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸዉ::
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግጋት፣ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ብቶች ስምምነቶችና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተመጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ::

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

## አንቀጽ 14

## የሕይወት የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት

ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገረሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት መብትና፣ ነጻነት አለዉ::

## አንቀጽ 15

## በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛዉም ሰዉ በሕይወት የመኖር መብት አለዉ:: ማንኛዉም ሰዉ በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም::

## አንቀጽ 16

## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛዉም ሰዉ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለዉ::

## አንቀጽ 17

## የነጻነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ ነጻነቱን አያጣም::
2. ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም::

## አንቀጽ 18

## ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛዉም ሰዉ ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለዉ::
2. ማንኛዉም ሰዉ በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም:: በማንኛዉም ዓላማና ሁኔታ በሰዉ የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነዉ::
3. ማንኛዉም ሰዉ በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛዉም ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ የተከለከለ ነዉ::
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ማሟላት የሚለዉ" ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም:-
   ሀ. ማንኛዉም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሰራ የተወሰዉን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራዉን ማንኛዉም ሥራ፣
   ለ. ማንኛዉም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናዉ የማይፈቅድለት ሰዉ በምትኩ የሚሰጠዉ አገልግሎት፣
   ሐ. የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማነኛዉም አገልግሎት፣
   መ. በሚመለከተዉ ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢዉ የሚፈፀምን ማነኛዉም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 19

## የተያዘ ሰዉ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ወንጀል ፈፅሚል ተብሎ በሚያዝበት ጊዜ የቀረበበት ክስና የተያዘበት ምክንያት በሚገባዉ ቋንቋ እንዲነገረዉ መብት አለዉ::
2. የተያዘ ሰዉ የተከሰሰበትን ጉዳይ በተመለከተ ያለመናገር መብት ያለዉ መሆኑ፣ ለመናገር ከመረጠ ደግሞ የሚሰጠዉ ቃል በፍርድ ቤት በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለዉ ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያዉኑ ማስገንዘቢያእንዲሰጠዉ መብት አለዉ::
3. ማንኛዉም የተያዘ ሰዉ በተያዘ በአርባ ስምንት ሰዓት ዉስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለዉ:: ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለዉ ግምት የሚጠይቀዉን ጊዜ አይጨምርም:: ወዲያዉኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበ በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለዉ::

4. የያዘዉ አካል ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነጻነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለዉ:: ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታዉ የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘዉ ሰዉ በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገዉን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚወስነዉ ኃላፊ የሆኑት ሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራዉን አጣርተዉ የተያዘዉ ሰዉ በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለዉን መብት በሚያስከብር መልኩ መሆን አለበት::

5. ማንኛዉም ሰዉ በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸዉንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደድም:: በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረዉም::

6. የተያዘ ሰዉ በዋስ የመፈታት መብት አለዉ:: ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል::

## አንቀጽ 20

## የተከሰሰ ሰዉ መብት

1. የተከሰሰ ሰዉ ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝቡ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለዉ:: ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ ወይም የአገሪቱን ወይም የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክር በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል:

2. የተከሰሰ ሰዉ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረዉና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አለዉ::

3. ማንኛዉም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለዉ:: በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለዉ::

4. የተከሰሰ ሰዉ የቀረበበትን ማንኛዉም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለዉ::

5. የተከሰሰ ሰዉ በመረጠዉ የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም ከሌለዉና ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለዉ::

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ተከሳሽ ቅሬታ ካለዉ ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል::

7. ተከሳሽ የፍርዱ ሂደት በማይገባዉ ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለዉ::

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለዉ::

2. ማንኛዉም የታሰረ ሰዉ ከትዳር ጓደኛዉ፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ ከኃይማኖት አማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞቹና ከሕግ አማካሪዎቹ ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙት እድል የማግኘት መብት አለዉ::

## አንቀጽ 22

## የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛዉም ሰዉ የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም:: እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ በነበረዉ የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛዉም ሰዉ ላይ አይወሰንም::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

## አንቀጽ 23

## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛዉም ሰዉ በወንጀለኛ መቅጫ ህግና ሥነ-ሥርዓት ወይም አግባብ ባላቸዉ ሌሎች ህጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ዉሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም::

## አንቀጽ 24

## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ በማንኛዉም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እዉቅና የማግኘት መብት አለዉ::

2. ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለዉ::

3. ማንኛዉም ሰዉ የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለዉ::

## አንቀጽ 25

## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸዉ፣ በመካከላቸዉ ማንኛዉም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል:: በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋና በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትዉልድ ወይም በሌላ በማንኛዉም አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ዜጎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ::

## አንቀጽ 26

## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ የግል ሕይወቱና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለዉ:: ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰዉነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታዉ ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል::
2. ማንኛዉም ሰዉ በግል የሚጽፋቸዉና የሚጻጻፍባቸዉ፣ በፖስታ የሚልካቸዉ ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች አይደፈሩም::
3. የመንግሥት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸዉ:: አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነት፣ የሕዝቡን ሰላም ለመጠበቅ፣ ወንጀል ለመከላከል፣ ጤናንና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር ዓላማዎች በወጡ ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም::

## አንቀጽ 27

## የኃይማኖት የሕሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛዉም ሰዉ የማሰብ፣ የህሊናና የኃይማኖት ነፃነት አለዉ:: ይህ መብት ማንኛዉም ሰዉ የመረጠዉን ኃይማኖት ወይም ዕምነት የመያዝ ወይም የመቀበል እና የኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ ወይም የመግለፅ፣ መብትን ያካትታል::
2. በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 90/2/ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የኃይማኖት ተከታዮች ኃይማኖታቸዉን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸዉ የኃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ::
3. ማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገዉን እምነት ለመያዝ ያለዉን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላዉ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም::
4. ወላጆችና ሌሎች ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸዉ መሠረት የኃይማኖታቸዉንና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸዉን የማሳደግ መብት አላቸዉ::
5. ኃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለዉ የሕዝብን ደኅንነት፣ ሰላምን፣ ትምህርትን፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግሥት ከኃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል::

## አንቀጽ 28

## በሰብእና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች በሰዉ ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለዉ የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰዉ ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመዉሰድ በአስገዳጅ ሰዉን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም:: በሕግ አዉጭዉ ክፍልም ሆነ በማንኛዉም የመንግስት አካል ዉሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም::

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 29

## የአመለካከት ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ያለማንኛዉም ጣልቃ ገብነት የመሰለዉን አመለካከት ለመያዝ ይችላል::
2. ማንኛዉም ሰዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለዉ:: ይህ ነፃነት በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጭ ወሰን ሣይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በኅትመት በሥነ-ጥበብ መልክ ወይም በመረጠዉ በማንኛዉም የማሠራጫ ዘዴ ማንኛዉንም ዓይነት መረጃና ሀሣብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል::
3. የፕሬስንና የሌሎችን መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል:: የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል::

   ሀ. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛዉም መልኩ የተከለከለ መሆኑን::

   ለ. የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን::

4- ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸዉን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረዉ የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል:

5- በመንግስት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ የአስተያየቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል::

6- እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸዉ የሚችለዉ የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለዉ የአስተሳሰባዊ ዉጤት ሊገታ አይገባዉም በሚል መርህ ላይ ተመስርተዉ በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል:: የወጣቶችን ደኅንነት የሰዉን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ:: የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናል::

## አንቀጽ 30

## የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ:: ከቤት ዉጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸዉ ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሰልፍ ሠላምን ዲሞክራሲያዊ

መብቶችንና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸዉ ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ::

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰዉን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም::

## አንቀጽ 31

## የመደራጀት መብት

ማንኛዉም ሰዉ ለማንኛዉም ዓላማ በማኀበር የመደራጀት መብት አለዉ:: ሆኖም አግባብ ያለዉን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሠረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ::

## አንቀጽ 32

## የመዘዋወር ነፃነት

በፌደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ዉስጥ የሚገኝ ሰዉ በፈለገዉ የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖር፣ ሐብት የማፍራትና የመያዝ እንዲሁም በፈለገዉ ጊዜ ከክልሉ የመዉጣት ነፃነት አለዉ::

## አንቀጽ 33

## በመንግሥታዊና ህዝባዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት

በክልሉ ዉስጥ ነዋሪ የሆነና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያዉቅ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በፌዴራሉና በዚህ ህገ መንግስት መሰረት በማንኛዉም የክልሉ መንግሥታዊ ወይም ህዝባዊ ሥራ ተቀጥሮ ወይም ተመርጦ የመስራት መብት አለዉ::

## አንቀጽ 34

## የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነ የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸዉ የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸዉ:: በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻዉ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸዉ:: በፍቺም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ::

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል::

3. ቤተሰብ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለዉ::

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረዉ መሠረት በኃይማኖት በባህል ሥርዓቶች ላይ ተመሥርተዉ ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እዉቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል::

5. ይህ ሕገ-መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፍቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 35

## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ-መንግሥት በአረጋገጣቸዉ መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸዉ::

2. ሴቶች በዚህ ሕገ-መንግሥት በተደነገገዉ መሠረት ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸዉ::

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸዉ የደረሰባቸዉን የታሪክ ቅርስ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸዉ በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸዉ:: በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኀበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነዉ::

4. ሴቶች ከጎጂ ባህል ተፅዕኖ የመላቀቅ መብታቸዉ መንግሥት ማስከበር አለበት:: ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸዉ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸዉ::

5. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች:-

   ሀ/ የወሊድ ፍቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸዉ፣ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል::

   ለ/ የወሊድ ፍቃድ በሕግ በሚወሰነዉ መሠረት፤ ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል::

6. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች እቅድና በፕሮጀክት ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸዉን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸዉ::

7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸዉ:: በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ ማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸዉ:: እንዲሁም ዉርሱን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸዉ::

8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸዉ::

9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክኒያት የሚደርስባቸዉን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸዉን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸዉ::

## አንቀጽ 36

## የሕፃናት መብት

1. ማንኛዉም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት

ሀ/ በሕይወት የመኖር፤

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፤

ሐ/ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸዉን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፤

መ/ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት በጤናዉና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠሩ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፤

ሠ/በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ዉስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን::

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አዉጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት::

3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተዉ መያዝ አለባቸዉ::

4. ከጋብቻ ዉጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ዉስጥ ከተወለዱ ህጻናት ጋር እኩል መብት አላቸዉ::

5. መንግሥት ለእጓለማዉታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል:: በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸዉንና ትምህርታቸዉን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል::

## አንቀጽ 37

## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ::

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉን ዉሳኔ ወይም ፍርድ፤

ሀ/ ማንኛዉም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፤

ለ/ ማንኛዉንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸዉን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለዉ::

## አንቀጽ 38

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማናቸዉም የክልሉ ሕዝብ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት::

ሀ/ በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸዉ ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፤

ለ/ ዕድሜዉ 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሠረት የመምረጥ፤

ሐ/ በዚሕ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 33 የተፃፈዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜያቸዉ ከ21 ዓመት ሲሞላዉ መመረጥ፤

መ/ ምርጫዉ ሁሉ አቀፍ፤ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር ድምፅ አስጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ በሐገራችን ሕገ-መንግሥትና በምርጫ ሕግ መሠረት መሆን አለበት::

2. ማንኛዉም ሰዉ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀዉን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ዉስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈፅማሉ::

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## አንቀጽ 39

## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብቶች

የሐረሪ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለዉ መብት በማናቸዉም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነዉ:: በዚህ መሠረት የሐረሪ ሕዝብ፤

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብ የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋዉ የመጠቀም፣ ቋንቋዉን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለዉ::

2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማከናወን ራሱን የመስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ዉስጥ በነፃነትና አድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ አግባብ ዉጤታማ ተሣትፎ ለማድረግ መብት አለዉ፤

3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በራሱ መልክአ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ዉስጥ ሚዛናዊ ዉክልና የማግኘት መብት አለዉ::

4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር /1/ /2/ እና /3/ የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ ተረገጡ፣ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና እነኝህም መብቶች በኢፌዴሪ መንግስት አንድነት ጥላ ሥር ሆኖ ሊያስተካክላቸዉ ባልቻለበት ጊዜ እስከ መገንጠል ድረስ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል፤

5. የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለዉ መብት በሥራ ላይ የሚዉለዉ፤

ሀ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

ለ/ የጉባኤዉ የመገንጠል ዉሳኔ በደረሰዉ በሶስት ዓመት ጊዜ ዉስጥ የፌዴራሉ መንግሥት ሕዝብ ዉሳኔ ሲያደራጅ፤

ሐ/የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ዉሳኔ በአብላጭ ድምጽ ሲደገፍ፤

መ/ የፌደራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለጠየቀዉ ለሐረሪ ሕዝብ ስልጣኑን ሲያስረክብና፤

ሠ/ በሕግ በሚወሰነዉ መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነዉ::

6. በዚህ ህገ መንግሥት ዉስጥ «የሐረሪ ህዝብ» ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸዉ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልዉና አለን ብለዉ የሚያምኑና የስነ ልቦና አንድነት ያላቸዉ በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖር ህብረተሰብ ማለት ነዉ::

## አንቀጽ 40

## የንብረት መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ይከበርላታል:: ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ/የማዉረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል::

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰዉነት በሕግ የተሰጣቸዉ ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸዉ ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸዉ ማኅበረሰቦች በጉልበታቸዉ፣ ፈጠራ ችሎታቸዉ ወይም በካፒታላቸዉ ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና ተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረዉ ዋጋ ያለዉ ዉጤት ነዉ::

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነዉ:: መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ::

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመነቀል መብታቸዉ የተከበረ ነዉ:: አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል::

5. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸዉን ያስከብርላቸዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

6. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገዉ ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለዉ:: ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማዉረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል:: ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል::

7. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመዉሰድ ይችላል::

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ወይም በክልሉ ዉስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ሥራ የመስራት መብት አለዉ::

2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያዉን፣ ሥራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ::

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸዉ::

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ ለማቅረብ በየጊዜዉ እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል::

5. የክልሉ መንግሥት አካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዉያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደዉ ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል::

6. የክልሉ መንግሥት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከታተላል፣ እንዲሁም በሚካሄደዉ የሥራ ዘርፍ ዉስጥ የስራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል::

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል::

8. መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት::

## አንቀጽ 42

## የሠራተኞች መብት

1- ሀ/ የፋብሪካ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠርሠራተኞችከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸዉ የሚፈቅድላቸዉ የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸዉ:: ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸዉን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል::

ለ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸዉን የማሰማት መብት አላቸዉ::

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እዉቅና ባገኙ መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወስናሉ::

መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ::

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜዉ ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸዉ የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸዉ::

3. እነዚህ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እዉቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት ሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋምበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ::

## አንቀጽ 43

## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸዉን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ::

2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትንም ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸዉን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸዉ::

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል::

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸዉ::

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸዉ ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዛዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸዉ::

## ምዕራፍ አራት

## የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45

## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት በክልል እና በቀበሌ የተዋቀረ ነዉ:: ይሁን እንጂ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሌሎች የአስተዳደር መዋቅሮች ሊያዋቅርና ሥልጣንና ተግባራቸውን ሊወስን ይችላል::

2. ሐረር ከተማ የራሱ አስተዳደር ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 46

## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አዉጪ አካል የሐረሪ ክልል ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለወከለዉ ሕዝብ ነዉ::

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ::

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነዉ::

## አንቀጽ 47

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ዉስጥ በግልጽ ተለይተዉ ለፌደራሉ መንግሥት ወይም ለፌደራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ዉጪ ያሉ ማናቸዉም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረዉ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት:-

   2.1. የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

   2.2. የክልሉን ህገ መንግሥትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

   2.3. የፌደራል መንግሥት በሚያወጣዉ ህግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል::

   2.4. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል:: የህግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትና ይህንን ህገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል::

   2.5. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ዉስጥ ማስገባት ይኖርበታል::

   2.6. ክልሉን ፖሊሲ ሀይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል::

   2.7. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌ እንደተጠበቁ ሆነዉ በህግ መሰረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል::

   2.8. ለክልሉ በተወሰነዉ የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል::

   2.9. በክልሉ መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል::

   2.10. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል::

   2.11. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል::

   2.12. በክልሉ በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል::

2.13. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የስራ ግብርና የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይሰበስባል::

2.14. ከፌደራሉ መንግሥት ጋር

ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁማቸዉ የልማት ድርጅቶች የሚገኘዉን የንግድ ትርፍ ግብር፣ ሥራ ግብር፣ የሽታጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛዉም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘዉን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሰረት ይካፈላል::

2.15. በክልሉ መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፍቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል::

2.16. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል::

2.17. በክልሉ ዉስጥ ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል::

## ምዕራፍ አምስት

## የክልሉ ም/ቤት አወቃቀርና፣ አወካከል ሥልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 48

### የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት 36 አባላት ያሉትና በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የክልል ም/ቤት ነዉ::

### አንቀጽ 49

### የም/ቤቱ ጉባኤዎች

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሁለት ጉባኤዎች:-

ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና

ለ/ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ናቸዉ::

2. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተዉ የሚወከሉ ሃያ ሁለት አባላት ይኖሩታል::

3. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 50 /2/ እንደተመለከተዉ የሚወከሉ 14 የሐረሪ ብሔረሰብ አባለት ይኖሩታል::

### አንቀጽ 50

### የጉባኤዎች አከፋፈል አወካከልና አመራረጥ

1. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላት ያሉት ጉባኤ ነዉ:: አወካከሉ:-

ሀ/ ከጀጎል ምርጫ ክልል 4 አባላትና

ለ/ ከጀጎል ዉጭ ካሉት የከተማ ቀበሌዎችና የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራትን የሚያጠቃልል የምርጫ ክልል 18 አባላት ይመረጣል::

2. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ዉስጥና ከክልሉ ዉጭ በሌላ በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል::

3. የጉባኤዉ አባላት ምርጫ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ ድምፅ በሚስጥር በመስጠት ስርዓት ይፈጸማል::

## ክፍል አንድ

## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

### አንቀጽ 51

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በጋራ የሚሰበሰቡበት ም/ቤት ነዉ:: በዚህ ህገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ህግ አዉጪና በክልሉ የዉስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነዉ::

2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ/ የክልሉን ሕገ-መንግስትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል::

ለ/ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 በተደነገገዉ መሠረት የክልሉን ሕገ-መንግስት ያሻሽላል::

ሐ/የፌዴራል ሕገ-መንግስት ለክልሎች የተሰጠዉን ስልጣን በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል::

መ/ለክልሉ ፕሬዝደንትነት በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ጠቋሚነት የሚቀርበዉን እጩ በ2/3ኛ ድምጽ መርምሮ ይመርጣል::

ሠ/ የክልሉን የዉስጥ አስተዳደር ያዋቅራል ያደራጃል::

ረ/ የክልሉን የሕዝብ ደህንነትና ፀጥታን በሚመለከት ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል::

ሰ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት የሚቀርቡለትን አዋጆች ደንቦች መመሪያዎችና ፖሊሲዎች መርምሮ ያፀድቃል::

ሸ/ በክልሉ ፕሬዝዳንት የቀረቡትን ም/ፕሬዝዳንት፣ የክልል አስፈፃሚ/ካብኔ/ አባል የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸዉን ኃላፊዎች ሹመት ያፀድቃል::

ቀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ምክትል ፕሬዝደንትና ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር ይሾማል::

በ/ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡትን ዳኞች ሹመት ያፀድቃል::

ተ/ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ያወጣል::

ቸ/ ለክልሉ በተሰጠዉ የገቢ ምንጭ ወሰን ግብርና ታክስ ይጥላል::

ነ/ የክልሉን አመታዊ በጀት ያፀድቃል::

ኘ/ በክልሉ ዉስጥ ማናቸዉም ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ያዉጃል::

አ/ የክልሉን መንግሥት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎች ያወጣል::

ወ/ በህጉ መሰረት ምህረት ያደርጋል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል:: የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል::

የ/ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈጻሚዉን አካል አሠራር ይመረምራል::

## አንቀጽ 52

## የም/ቤቱ አመራርና አሠራር

1. ም/ቤቱ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይኖሩታል::
2. እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል::
3. አፈ-ጉባኤዉ በህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በኩል እንዲሁም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በኩል ቀርበዉ በምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምፅ ይመረጣሉ::

## አንቀጽ 53

## የአፈ-ጉባኤዉ ስልጣንና ተግባር

1. የም/ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል::
2. የም/ቤቱን ጠቅላላ ሥራዎች ያስተዳድራል::
3. በም/ቤቱ አባላት ላይ የሚወሰኑ የዲሲፒሊን እርምጃዎችን ያስፈጽማል::
4. የአፈ-ጉባኤዉ ሌሎች ሥራዎች በዝርዝር የሚወጣ ሌላ ሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 54

## የምክትል አፈ-ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

1. በአፈ-ጉባኤ ተለይቶ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል::
2. አፈ-ጉባኤዉ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 55

## የም/ቤቱ አባላት መብትና ግዴታ

1. ማንኛዉም የም/ቤቱ አባል በም/ቤቱ በሚሰጠዉ ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም::
2. ማንኛዉም የም/ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ም/ቤቱ ፍቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም::
3. ማንኛዉም የም/ቤቱ አባል የመረጠዉ ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ከም/ቤት አባልነት ይወገዳል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 56

## የም/ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. ም/ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::
2. የም/ቤቱ አባላት የሥራ ዘመን ለአምስት አመት ነዉ:: የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞዉ ም/ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ዉስጥ አዲሱ ም/ቤት ሥራዉን ይጀምራል::
3. የም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤት አባላት መካከል ከ1/3ኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠሩ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤዉ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::
4. የም/ቤቱ ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል:: ሆኖም ስብሰባዉ በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ከተጠየቀና ከም/ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄዉን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል::

## አንቀጽ 57

## የዉሳኔ አሰጣጥና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች

1. ከም/ቤት አባላት መካከል ከ2/3ኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
2. ማንኛዉም ዉሳኔ የሚተላለፈዉ በም/ቤቱ ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይሆናል::
3. ምክር ቤቱ አሰራሩንና የሕግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ሕጎችን ሊያወጣ ይችላል::

## ክፍል ሁለት

## የጉባኤዎች ስልጣንና ተግባር

## አንቀጽ 58

## የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በክልሉ ም/ቤት ከሚኖረዉ ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. ማንኛዉም የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂ በተመለከተ ረቂቅ ሕግ ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያጸድቃል::
2. የግብርና ታክስ አዋጆችን ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያጸድቃል::
3. የክልሉን በጀት ገምግሞ ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል:
4. በክልሉ የም/ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤነት አንድ አባል ይጠቁማል::

5. የጉባኤዉን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና

6. ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል::

## አንቀጽ 59

## የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ብሔረሰብ ቋንቋና ባሕል በሚመለከት ፖሊሲና ሕግ ያወጣል::

2. በክልሉ ዉስጥ የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪክና ባሕል የሚያንጸባርቁ ቅርፃቅርፆች የመቃብር ቦታዎች የመስኪድና የአድባራት አጠባበቅን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል::

3. የሐረሪ ብሔረሰብ በፌዴራል መንግስት የፌድሬሽን ም/ቤት በሚወከሉ ወይም የሚወከሉ አባል ወይም አባላትን ይመርጣል::

4. የክልሉን ፕሬዝዳንትና የም/ቤቱን ምክትል አፈ-ጉባኤ ይጠቁማል::

5. የጉባኤዉን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል ጉባኤና

6. የጉባኤዉን ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል::

7. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 39 መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል::

## ምዕራፍ ስድስት

## የክልሉ መስተዳደር ምክር በ፡ት

## አንቀጽ 60

## ስለ አስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠዉ ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ነዉ::

2. የመስተዳደሩ ም/ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ዉሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ::

## አንቀጽ 61

## የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ፕሬዝዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቱ፣ የቢሮ ኃላፊዎችና የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚወስናቸዉ ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነዉ::

2. ፕሬዝደንቱና የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በዚህ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የሚሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል::

3. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ሰብሳቢ ፕሬዝደንቱ ይሆናሉ::

4. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል::

## አንቀጽ 62

## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በፌዴራል ሕገ-መንግስት የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል::

1. በፌዴራል መንግስት፣ በክልሉ ምክር ቤት እና በሐረሪ ጉባኤ የወጡት ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል::

2. የክልሉን የመስተዳደር አካላትና ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል::

3. የክልሉን ማሕበራዊ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል::

4. የክልሉን መስተዳደር ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል::

5. የክልሉን ቢሮዎችና አስፈፃሚ አካላት ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል::

6. ህግና ስርአት በክልሉ መከበሩን ያረጋግጣል::

7. የልማት፣ የማህበራዊ ጉዳይ ጸጥታና ደህንነትን በሚመለከት የህግና የፖሊሲ ረቂቆችን ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያዉላል፤

8. በክልሉ ም/ቤት በሚሰጠዉ ስልጣን መሰረት ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል::

9. ስለ ስራዉ እንቅስቃሴ ለክልሉ ም/ቤት ሪፖርት ያቀርባል::

10. በምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

11. በዚህ ሕገ-መንግስት መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያዉጃል::

12. በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በሕግ ሊያዋቅር ይችላል::

## አንቀጽ 63

## የፕሬዝዳንቱ አሰያየም

1. ፕሬዝዳንቱ በሀረሪ ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ም/ቤት የሚመረጥ ይሆናል::

2. የፕሬዝዳንቱ የስራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የስራ ዘመን ይሆናል::

3. ፕሬዝዳንቱ በምክር ቤቱ ፊትለፊት ቃለመሀላ መፈጸም ይኖርበታል:: የቃለመሀላዉ ይዘት እንደሚከተለዉ ይሆናል::

   «እኔ ______በዛሬዉ ዕለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ሃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁኝ»

## አንቀጽ 64

## የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል::

ለ/ የክልሉ ም/ቤት የሐረሪ ጉባኤ እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚያወጡአቸዉን ህጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ዉሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፤ ያስፈፅማል::

ሐ/ የክልሉን ም/ፕሬዝዳንት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንቱን፣ ዋና ኦዲተር፣ ም/ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር፣ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላትና ሌሎች የክልሉ መስሪያ ቤቶች ሀላፊዎችን ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያሾማል::

መ/ በንዑስ አንቀጽ /ሐ/ ሥር የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ም/ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ሃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል::

ሠ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ዉጪ የሆኑ ሃላፊዎች ም/ቢሮ ሃላፊዎች ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ሃላፊዎችን ይሾማል::

ረ/ የካቢኔ አባላት፣ የቢሮ ሃላፊዎች ወይም የጽ/ቤት ሃላፊዎች ችግር ስኖርባቸዉ በማገድና ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያስወግዳል::

ሰ/ የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ህግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊሲ ሀይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል::

ሸ/በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል::

## *አንቀጽ 65*

## *የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት*

ፕሬዝዳንቱ በዚህ ህገ መንግስትና በሌሎች ሕጎች የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 66

## የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

ሀ. በክልሉ ፕሬዝዳንትና በክልል መስተዳድር ም/ቤት የሚሰጡት ተግባራትን ያከናዉናል::

ለ/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ስልጣን

## አንቀጽ 67

## ስለ ነጻ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ-መንግስት ተቋቁሟል::
2. የዳኝነት ስልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠዉ ተቋም ዉጭ የሚያደርግና በህግ የተደነገገዉን የዳኝነት ስርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም::

## አንቀጽ 68

## ስለ ባህላዊና ኋይማኖታዊ ዳኝነት

1. የሀይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በሚወጣ ዝርዝር ህግ መሰረት ሊቋቋሙ ወይም ዕዉቅና ሊሰጣቸዉ ይችላል::
2. ይህ ህገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት ዕዉቅና አግኝተዉ ሲሰራባቸዉ የነበሩ ሀይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ህገ መንግሥት እዉቅና አግኝተዉ ይደራጃሉ::

## አንቀጽ 69

## የዳኝነት ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነዉ::
2. በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸዉም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተጽእኖ ነጻ ነዉ::
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነፃነት ያከናዉናሉ፤ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም::
4. ማንኛዉም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነዉ የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ዉጭ ከዳኝነት ስራዉ አይነሳም::

   ሀ/የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፒሊን ህግ መሰረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፤

   ለ/በህመም ምክንያት ዳኛዉ ተግባሩን በተገቢዉ ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፤

   ሐ/የጉባኤዉ ዉሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ አብላጫ ድምጽ ተደግፎ ሲጸድቅ::

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ስራዉ የሚያስነሳዉ ጥፋት ፈፅሟል ብሎ ጉባኤዉ ካመነበት ጉዳዩ በክልሉ ም/ቤት እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ስራዉ ይፉገዳል::
6. የማንኛዉም ዳኛ የጡረታ መዉጫ ጊዜ አይራዘምም::

## አንቀጽ 70

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይደራጃል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

   ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛዉና

   የመጨረሻዉ የዳኝነት ስልጣን፤

   ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና፤

   ሐ/ ማንኛዉም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠዉ የመጨረሻ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡
3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ስልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፡፡
7. የክልሉ ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በዉክልና ለሚሰሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግስት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል፡፡

## አንቀጽ 71

## የዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሮዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዕጩዎቹ ላይ ያለዉን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀዉን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የዕጩ ዳኞች ሹመት ያፀድቃል፡፡

## አንቀጽ 72

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ዉስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል፡፡
2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የጉባኤዉ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
3. የጉባኤዉ አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 73

## ህገ መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. የህገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን ዉሳኔ ያገኛል፡፡
2. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሰላሳ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡
3. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ/ በኢፌድሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት የሐረሪ ተወካይ ሰብሳቢ

   ለ/ በኢፌድሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐረሪ ክልል ተወካዮች መካከል አንደኛዉም ምክትል ሰብሳቢ ሁለተኛዉ ፀሐፊ ሆነዉ በኮሚሲዮኑ ይመረጣሉ፡፡

   ሐ/ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሐረሪ ጉባኤና በሐረሪ ህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ከእያንዳንዱ ጉባኤ የሚወከሉ ሁለት ሁለት ተወካዮች አባላት፡፡

   መ/ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቀድሞ ፕሬዝዳንት/ፕሬዝዳንቶች/ ድምጽ ሳይሰጡ የሚሳተፉበት፡፡

## አንቀጽ 74

## የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
2. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፣
3. አባላቱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

   ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ...........ሰብሳቢ፣

   ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ...........ምክትል ሰብሳቢ፣

   ሐ/ በክልሉ መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸዉና በሥነ-ምግባራቸዉ የተመሰከረላቸዉ ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፣

   መ/ በአፈ-ጉባኤዉ አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል የሚሰየሙ 3 ተወካዮች፣

4. የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ህገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገዉ ማጣራት መሰረት ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በጉዳይ ላይ የዉሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

ለ/ በክልሉ ህግ አዉጪ አካል የሚወጡ ህጎች ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ዉሳኔ ለህገ መንግሥት ተርጓሚዉ ኮሚሲዮን ያቀርባል።

ሐ/ በፍርድ ቤቶች የህገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ

1. ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘዉ ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪዉ ጉባኤ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታዉን ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

2. የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ለመጨረሻ ዉሳኔ ያቀርባል።

መ/ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

## ምዕራፍ ስምንት

## አንቀጽ 75

## ስለቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻዉ መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ነዉ።

2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል

ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፣

ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ/ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸዉ።

3. የቀበሌ መስተዳድር አካላት አደረጃጀትና ሥልጣንና ሃላፊነታቸዉን በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወጣል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 76

## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1. ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ ቁጥር 11 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል።

2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉን አዉጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ዉስጥ አፈ-ጉባኤዉ ምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስጸደቅ አለበት።

3. የመስተዳድር ምክር ቤት ያወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለዉ ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወሰን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉ በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል።

4. የመስተዳደሩ ምክር ቤት እና ም/ቤቱ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸዉ ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 14፣ 16፣ 18//1/ እና 2፣ 21/1/፣ 24፣ 1/25፣ 27/1/ እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸዉም።

5. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል። ቦርዱ በፌደራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 /6/ የተጠቀሱት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

## አንቀጽ 77

## የክልሉ ፖሊሲ ዓላማዎች

ማንኛዉም የመንግሥት አካል የፌደራሉንና የክልሉን ሕገ-መንግሥት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ ሲያውል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ምዕራፍ 10 አንቀጽ 85 እስከ አንቀጽ 92 የተመለከቱትን ብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ነው።

## አንቀጽ 78

## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል።

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልሉ መንግሥት የተመደበዉ ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።

## አንቀጽ 79

## የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብን ስለማመንጨትና ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ 3 ድንጋጌዎች በፌደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 105 ከተደነገገዉ ዉጭ ሊሻሻሉ አይችልም።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተዘረዘሩት ዉጭ ያሉት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት፡-

ሀ/ የህገ መንግሥቱ የማሻሻያ ሐሳብ ከሁለቱ ጉባኤዎች ቢያንስ በአንዱ ሲነሳ

ለ/ የማሻሻያ ሃሳቡ በሁለቱም ጉባዔዎች ለየብቻቸዉ ዉይይት ተደርጎበት ከእያንዳንዱ ጉባኤ በ2/3 ድምፅ ሲደገፍ እና

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት ማሻሻያዉን በ2/3ኛ ድምፅ ሲያጸድቅ ብቻ ነዉ፡፡

## አንቀጽ 80

### ሕገ-መንግሥቱ የሚታተምባቸዉ ቋንቋዎች

ይህ ሕገ-መንግሥት በሐረሪኛ፣ በኦሮምኛና በአማረኛ ቋንቋዎች ይታተማሉ ፡፡ በሐረሪ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች መካከል የትርጉም ልዩነት ሲኖር የአማረኛ ቅጂ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡